ይናፍቁ ጀመር፡፡ በኦሪት ዘመን የነበረው ይህ ክቡር ቅርስ በራሱ በእግዚአብሔር ምርጫ በትግራይ ተራራማ ቦታ ይቀመጥ ዘንድ ስለመመረጡ አፈታሪኮቹ በምሥጢራዊ መልእክት አዘል ጽሑፍ መልክ በክብረ ነገሥት ተጻፉ፡፡ በክብረ ነገሥት ውስጥ የተጠቀሱት የዘመን አቆጣጠሮች የተሳሳቱና የተቃረኑ ቢሆኑም የኋለኛው ዘመን ምሁራን ከነዚህ የማይጨበጡ ከሚመስሉ አፈታሪኮች በስተጀርባ ያለውን ሥውር እውነታ ለማየት አልቻሉም፡፡

ይህ እውነታ ግን አስቀድሞ በቴምፕላሮች በመታወቁ የቃል ኪዳኑን ታቦት ምድር የሚያናውጥ ኃይል የተረዱ በመሆናቸው ዱካውን ተከትለው ወደኢትዮጵያ መጥተዋል፡፡ በተጨማሪም ዎልፍራም ቮን ኢስከንባኽ በፓርዚቫል ታሪኩ ውስጥ ስለቅዱሱ ጽዋ "ዒፈቃደ ልብ ተፍጻሜት" በማለት ስለቃል ኪዳኑ ታቦት ምሥጢራዊ በሆነ ዘዴ ጽፏል፡፡

በዎልፍራም ውስጥ አረማዊው ፍሌጀታኒስ ስለሰማይ ከዋክብት ስብስብ የተደበቀውን ምሥጢር ጠልቆ ከተረዳ በኋላ ታላቅ ክብሬታ በተሞላ አንጋገር "ጽዋ የተባለ ነገር" አለ ብሏል፡፡ በተጨማሪም ይህ ድንቅ ነገር፣ ይህ መንፈሳዊ የሆነ ነገር፣ ንጹሕ ሕይወት ባለው የክርስቲያን ልጅ እንደሚጠበቅም አሳውቋል፡፡ እናም በሚያጽናና ቃል ሲደመድመው፣ "ወደዚህ ጽዋ የተጠሩ ሰዎች የተመሰገኑ ናቸው"[15] እንዲሁም ወደቃል ኪዳኑ ታቦት የተጠሩ ሰዎች፣ ታቦቱና ጽዋው አንድ ናቸውና ይላል፡፡

እኔ ለራሴ ለዚህ የተገባሁ አይደለሁም፡፡ ገና በረሃውን እያቋረጥኩ እያለሁ አውቄዋለሁ፡፡ ወደማደሪያው ቤተመቅደስ እንደቀረብኩም አውቄዋለሁ፡፡ አሁንም አውቃለሁ፡፡ ይህም ቢሆን ግን ... "ልቤ ደስተኛ ነው፤ ነፍሴ ትደሰታለች፤ ሥጋዬም እንደዚሁ በተስፋ ታርፋለች፡፡"

